የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሃያ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፵፭
አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፰ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29 thYear No. 45
ADDIS ABABA 24th August, 2021

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፻፳፩/፪ሺ፲፫

ሕገ-ወጥነትን ለሚጠቁሙ መረጃ አቅራቢዎች ስለሚሰጥ ማበረታቻ የወጣ ደንብ ገጽ----፪ሺ፵፮

REGULATION NO. 121/2021

INCENTIVES PROVISION FOR INFORMERS THAT REPORT ILLEGAL ACTIVITIES

Page---------------------------2246

## ደንብ ቁጥር ፻፳፩/፪ሺ፲፫

## ሕገ-ወጥነትን ለሚጠቁሙ መረጃ አቅራቢዎች ስለሚሰጥ ማበረታቻ የወጣ ደንብ

ሕገ-ወጥ የመሬት ይዞታ መስፋፋትና ሕጋዊ ባልሆነ የመሬት ይዞታ ግንባታ ማከናወን ከተማን በዕቅድና በሥርዓት ለማሳደግ የሚደረግ ጥረትን የሚያደናቅፍና ጤናማ የከተማ ሕይወትን የሚያደክም በመሆኑ፤ ከአስተዳደሩ ቤቶች በሕገ-ወጥ መንገድ ደሃውን ሕብረተሰብ እያፈናቀሉ ወደ ግል ይዞታነት ወይም ባለቤትነት ማዛወር የሕዝብ ሀብት በሆነው የከተማ መሬት፣ ይዞታና ቤት ላይ ያለአግባብ መበልጸግ በመሆኑና ይህም በከተማችን እየተስፋፋ የመጣውን የሌብነት፣ የማጭበርበር ወንጀል መከላከልና ሕጋዊ እርምጃ በከተማ አስተዳደሩ እየተወሰደ ቢሆንም ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት በሕዝብ ተሳትፎ ወንጀሉን የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባር መከናወን እንዳለበት በመታመኑ፤

## REGULATION NO. 121/2021

## INCENTIVES PROVISION FOR INFORMERS THAT REPORT ILLEGAL ACTIVITIES REGULATION NO. 121/2021

**WHEREAS,** it has been found necessary to prevent and contral illegal activities and crimes with the participation of the society and to solve the problem sustainably as the illegal landholding and construction activities have been increasing and such in turn hinders the efforts to develop the city in a planned and organized manner and affects the urban livelihood; as the illegal transfer of houses of the administration to private holdings or ownership by displacing the poor in an act of improper prosperity by using the land, holdings and houses of the city which are the property of the people and such theft and treachery has been escalating in the city even if the city administration has been precluding and taking lawful measures;

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

በከተማው ወስጥ በመሬት ወረራ፣ በህገወጥ የይዞታ ማስፋፋት፣ በሕገ-ወጥ ግንባታ፣ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የመንግሥት ቤቶችን ወደ ግል በማዞር ተግባር ላይ የተሳተፉ ሰዎችን ተጨባጭ ጥቆማ በማቅረብና በማጋለጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማበረታታትና ለጥቆማ አቅራቢዎችም ስለሚሰጥ ማበረታቻ ግልጽ የሆነ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ሕገ-ወጥ ተግባሩን በሕዝብ ተሳትፎና ቅንጅት መከላከል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፷፬/፪ሺ፲፩ (እንደተሻሻለ) አንቀፅ ፺፭ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

**፩ አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "ሕገ-ወጥነትን ለሚጠቁሙ መረጃ አቅራቢዎች ስለሚሰጥ ማበረታቻ የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፳፩/፪ሺ፲፫ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪ ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩ **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፪ **"አዋጅ"** ማለት የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፯፻፳፩/፪ሺ፬ ነው፤

፫ **"ጽህፈት ቤት"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ጽህፈት ቤት ነው፤

**WHEREAS,** it has been found necessary to prevent illegal activities through the participation of the public in an integrated manner by establishing an apparent systematic procedure for the provision of incentives for informers that present reports and encourage them to bring tangible reports and participate them in the process of unveiling those individuals who involved in the illegal transfer of government houses to private ownership, illegal construction, illegal expansion of landholdings and land grabbing activities in the city;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 95 of the Addis Ababa city government executive organs re-establishment and to specify the power and duties of the thereof Proclamation No. 64/2019 (as amended), the Addis Ababa city cabinet has issued this Regulation as follows.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as: "Incentives Provision for Informers that Report Illegal Activities Regulation No.121/2021."

2. **Definition**

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1. **"Government"** means the Addis Ababa City Government;
2. **"Proclamation"** means the Urban Lands Lease Holding Proclamation No.721/2011;
3. **"Office"** means Mayor's Office of the Addis Ababa City;

፬. **"ሕገወጥ የይዞታ መስፋፋት"** ማለት በሕጋዊ መንገድ የከተማው አስተዳደር ቦታን በይዞታነት እንዲያስተላልፍ ሥልጣን ከተሰጠው አካል በተገነባ ይዞታ በተጨማሪነት ከጎን ያለን ቦታ መከለልና መያዝ ነው፤

፭. **"ሕጋዊ ያልሆነ ይዞታ"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ ክልል የከተማ ቦታ ለተለያየ አገልግሎት እንዲመድብ በሕግ ኃላፊነት ከተሰጠው አካል እውቅና ውጭ የተገዛና በእጅ መናኛ የተያዘ ቦታ ነው፣

፮. **"ሕጋዊ ባልሆነ ይዞታ የተደረገ ግንባታ"** ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፭) በተጠቀሰው በተስፋፋ ሕገወጥ ይዞታ ወይም ሕጋዊ ባልሆነ ይዞታ የተካሄደ ግንባታ ነው፤

፯. **"የከተማ ፕላን"** ማለት ሥልጣን ባለው አካል የፀደቀና ህጋዊ ተፈፃሚነት ያለው የከተማ መዋቅራዊ ፕላን፣ የአካባቢ ልማት ፕላን ወይም መሠረታዊ ፕላን ሲሆን አባሪ የፅሁፍ ማብራሪያዎችን ይጨምራል፤

፰. **"መረጃ"** ማለት መረጃ አቅራቢው መሬት መወረሩን፣ በሕገ-ወጥ መንገድ ከተሰጠው ይዞታ ውጭ ይዞታ መስፋፋቱን፣ ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖር ግንባታ መገንባቱ፣ በህገ ወጥ መንገድ የመንግሥት ይዞታ ወይም ቤት ወደ ግል መዞሩን እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ሲፈጸሙ መገኘታቸውን የሚያመለክት መረጃ ነው፤

፱. **"ተጨባጭ መረጃ"** ማለት መረጃ አቅራቢው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ መሠረት በትክክል ተግባሩ እየተከናወነ ወይም የተከናወነ መሆኑን የሚጠቁምና አግባብ ባለው አካል ትክክለኝነቱ የሚረጋገጥ ነው፤

4. **"Illegal Expansion of Holdings"** means enclosing and possessing a nearby plot of land in addition to construction on a landholding given by an organ that was given the authority to legally transfer the landholdings of the city government;

5. **"Illegal Landholding"** means land which is bought and possessed without the knowledge of the relevant organ that has the legal authority to allocate an urban land for various purposes within the environs of the Addis Ababa City;

6. **"Construction on Illegal Holdings"** means a construction which is undertaken on an illegal expansion of holdings or on an illegal landholding pursuant to Sub-Article (4) and (5) of this Article;

7. **"Urban Plan"** means an approved and legally applied, structural plan, local development plan or basic plan of the city, by the concerned authorized organ; and it includes additional descriptive writings;

8. **"Information"** means information that the informer indicates the occurrence of land grabbing, illegal expansion of land beyond what was permitted, construction without a legal permit, the illegal transfer of a public landholding or house to a private one, and other related activities;

9. **"Tangible Evidence"** means the evidence that the informer reports that illegal activity is being carried out or was undertaken according to Article 7 of this Regulation and its correctness shall be verified by the relevant organ;

፲ **“ማበረታቻ”** ማለት በዚህ ደንብ መሠረት በሚቀርብ መረጃ መሰረት መረጃ አቅራቢው ያቀረባቸው መረጃዎች በዚህ ደንብ አንቀጽ፮ መሠረት የተዘረዘሩት ጥፋቶች መፈጸማቸውን የሚያረጋግጥ ጥቆማ መሆኑ አግባብ ባለው አካል ሲረጋገጥ ለመረጃ አቅራቢው የሚሰጥ ገንዘብ ነው፤

፲፩ **“መሠረታዊ የንግድ ዕቃ”** ማለት በገበያ ላይ እጥረት በመፈጠሩ ምክንያት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ሥራ ውድድር ሊያስከትል የሚችል ከሸማቾች የየዕለት ፍላጎት ጋር የተገናኘ የንግድ ዕቃ ሆኖ፣ በሚመለከተው አካል መሠረታዊ የንግድ ዕቃ ተብሎ በሕዝብ ማስታወቂያ የሚገለጽ የንግድ ዕቃ ነው፤

፲፪ **“አግባብ ያለው አካል”** ማለት በፌደራል ወይም በከተማ አስተዳደሩ ህጎች በየደረጃው የመንግሥት ተግባራትን የሚያከናውን ሥልጣን የተሰጠው አስፈጻሚ አካል ነው፤

፲፫ **“የንግድ ዕቃ ማከማቸት”** ማለት የንግድ ዕቃዎች ወይም ምርቶችን ሆን ብሎ የገበያ እጥረት እንዲፈጠር ወይም የገበያውን ዋጋ ለማናር በማሰብ በንግድ መደብሩ ወይም በማናቸውም ቦታ የንግድ ዕቃዎችን ወይም ምርቶችን በብዛት ማከማቸት ነው፡፡

፫ **<u>የፆታ አገላለጽ</u>**

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡



10. **"Incentive"** means cash that will be given to an informer, based on the information presented in accordance with this Regulation, that brings information that depicts the occurrence of the violations enlisted under Article 6 of this Regulation; and such report shall be verified by the relevant organ;
11. **"Basic Merchandise"** means business goods that are related to the daily demands of consumers that causes inappropriate business competition due to its lack of supply in the market, and described as basic merchandise by the relevant organ through public notice;
12. **“Relevant Organ”** means an executive body that has the authority to undertake the duties of the government at every level based on the laws of the federal or the city government;
13. **“Accumulation of Merchandise”** means the immense accumulation of business goods or products in a business store or at any place in order to create a deliberate shortage in the market or to increase the market price of the thereof.

**3. <u>Gender Expression</u>**

In this Regulation, any expression in the masculine gender shall include the feminine.

**፬ የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በከተማው አስተዳደር ክልል ውስጥ በመሬት ወረራ፣ በሕገ-ወጥ ይዞታ መስፋፋት፣ በህገወጥ ግንባታ፣ የመንግሥት ቤትን ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ወደ ግል ይዞታነት መቀየር፣ መሰረታዊ የንግድ እቃዎች ላይ ህገወጥ ተግባር መፈጸም፣ ሕገ-ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውር፣ በህገወጥ መንገድ የውጭ ምንዛሬ ማዘዋወር፣ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ገንዘቦችን በማተምና በማሰራጨት የማጭበርበር ወይም የማታለል ተግባር ላይ የተሳተፉትን በሚጠቁም እና ተጨባጭ መረጃ በሚሰጥ ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**፭ ዓላማ**

፩ ህገ-ወጥ ተግባርን በነዋሪው ተሳታፊነት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያግዝ የጥቆማ አቀራረብና ለመረጃ አቅራቢዎች የማበረታቻ አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት፤

፪ የተዘረጋውን ሥርዓት በጥብቅ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡

**ክፍል ሁለት**

**ተጨባጭ መረጃ የሚቀርብባቸው ሕገ-ወጥ ተግባራት እና የጥቆማ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት**

**፮ ተጨባጭ መረጃ የሚቀርብባቸው ሕገ-ወጥ ተግባራት**

፩ አግባብ ያለው አካል ሳይፈቅድ ማንኛውንም የከተማ መሬት መያዝ ወይም መውረር ወይም በመሬት ባንክ ተይዘው የነበሩ ይዞታዎችን ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ መያዝ፤

፪ አግባብ ያለው አካል ፈቃድ ሳያገኝ በሕጋዊነት ከያዘው ይዞታ ጎን ያለን የከተማ ቦታ አስፋፍቶ መከለልና መጠቀም ወይም ማጠር ወይም ከአዋሳኝ ይዞታ ጋር መቀላቀል፤

**4. Scope of Application**

This Regulation shall be applicable to individuals that reports and presents tangible evidence on those who participate in activities of land grabbing, illegal expansion of landholdings, illegal construction, illegal transfer of government houses to private ownership, carry out illegal activities on basic merchandise, illegal dealings of firearms, illegal circulation of foreign currencies, activities of treachery or deception by printing and distributing local and foreign currencies in the vicinity of the city government.

**5. Objective**

1. Establish report presentation and a system for the provision of incentives for informers so as to prevent and control illegal activities through the participation of the public;
2. Implement the created system effectively.

**PART TWO**

**ILLEGAL ACTIVITIES THAT DEMAND TANGIBLE EVIDENCE AND REPORTING PROCEDURE**

**6. Illegal Activities that Demand Tangible Evidence**

1. Seizure or grabbing of any urban land without the permission of the relevant organ or expropriation of landholdings that are in the hands of the land band;
2. Using an urban land, which is adjacent to a legally occupied land, through expansion and enclosing or by making fences or combine it with a nearby landholding;

፫. በአካባቢ ልማት ፕላን መሠረት ለመንገድ አውታር፣ ለማህበራዊ ተቋማትና ለአረንጓዴ ሥፍራዎች አገልግሎት እንዲውሉ የተከለሉ ቦታዎችን በሕገ ወጥነት መያዝ፤

፬. ለአካባቢ ጥበቃና ለአረንጓዴ ልማት፣ ፓርክ፣ የመንግሥት ይዞታዎች እና ለተለያየ አግልግሎት ተለይተው በተቀመጡ ባዶ ቦታዎች ላይ አግባብ ያለው አካል ሳይፈቀድ ለእቃ ማስቀመጫም ሆነ ሌላ ማንኛውም አግልግሎት አለአግባብ መያዝ፤

፭. በግልጽ ባለቤት ሳይኖራቸው በህገ-ወጥ መንገድ ተገንብተው ያሉ ሕንጻዎች እና ታጥረው የተያዙ ባዶ ቦታዎችን ይዞ መገኘት፤

፮. በመንግስት ይዞታ ሥር የሚተዳደሩ ቤቶች፣ ሼዶችና ሌሎች ማንኛውም ይዞታዎችን በተሳሳተ ሰነድ ስም ማዞር ወይም ለማዞር መሞከር፤

፯. ከአዋጁ ውጪ የከተማ መሬትን መፍቀድ ወይም ማስተላለፍ ወይም ክልከላ እያለበት የይዞታ ምስክር ወረቀት ካርታ መስጠት ወይም ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ ይዞታ ማረጋገጥ ወይም የአርሶ አደር የሆነውን ይዞታ ለማይገባው ሰው መብት እንዲፈጠር ማድረግ፤

፰. በሀሰተኛ ሰነድ የተዘጋጁ ካርታዎች፣ የግንባታ ፈቃዶች እና መሰል የመሬትና መሬት ነክ መረጃዎች ይዞ መገኘት ወይም ሀሰተኛ ሰነዶችን መሠረት አድርጎ ህገ-ወጥ ተግባር መፈጸም፣

፱. በመሬት፣ በመሬት ነክ እና በማናቸውም አስተዳደር አካላት ላይ የተመደበ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ጉቦ ሲቀባበል መገኘት፤

3. The illegal seizure of lands that are demarcated for the purpose of road infrastructure, social institutions, and green areas on the local development plan;

4. Inappropriate seizure of designated vacant spaces for the purpose of environmental protection and green development, parks, public holdings and for various services and use same for storage or any other purposes without the permission of the relevant organ;

5. Seizure of buildings that are illegally constructed, without having an identified ownership, and protected and occupied vacant spaces;

6. Naming transfer of houses, sheds, and any other holdings that are under the administration of the government using fraud documents or an attempt to do the same;

7. In contrary to the Proclamation, granting or transferring of urban lands or giving landholding certificate despite having restrictions or illegally verifying landholdings or create rights for an ineligible individual on the holdings of a farmer;

8. Possessing maps, construction permits, and similar land and land-related documents that are prepared using fraud documents or committing illegal activities based on fraud documents;

9. When an assigned official or employee on land, land-related and any other administrative organ receives a bribe for his own benefit or to benefit another person and caught;

፲. አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያን ሳይከተል መሬትን በሊዝ ወይም በምደባ እንዲገኝ ሕጋዊ አስመስሎ መሬት እንዲዘጋጅ ወይም እንዲመደብ ወይም እንዲተላለፍ ለሥራ ኃላፊዎች ወይም ለመወሰን ስልጣን ለተሰጣቸው አካላት የተሳሳተ ሰነድ ወይም መረጃ ወይም አድሏዊ አሰራር በመከተል አቅርቦ በተሳሳተ መንገድ ማስወሰን ወይም መወሰን፤

፲፩ ማንኛውም በከተማ ቦታ ሊዝ ጨረታ የሚወዳደር ሰው የሀሰት ማስረጃ ካቀረበ ወይም እንዲያቀርብ ድጋፍ ካደረገ፣ መግለጽ የነበረበትን መረጃ ከደበቀ ወይም ከሌላ ተወዳዳሪ ጋር በመመሳጠር የሀሰት ውድድር ካደረገ፤

፲፪ አግባብ ካለው የህግ ድንጋጌ ውጭ ግንባታ ያላረፈበትን ባዶ ቦታ ለስም ዝውውር ወይም ለሽያጭ ማቅረብ ወይም ባዶ ቦታ መሆኑ እየታወቀ ሥም ዝውውር ለማድረግ ሙከራ ማድረግ ወይም ሽያጭ እንዲከናወን ማድረግ፤

፲፫ በስም ዝውውር መክፈል የሚገባውን የአሹራ፣ የቴምብር ቀረጥ፣ የካፒታል ጌይን እና ሌሎች የአገልግሎት ክፍያዎች ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ቀንሶ ማስከፈል፤

፲፬ የይዞታ ማህደሮችን ወይም ከማህደር መረጃ ማጥፋት ወይም አግባብነት የሌለው አዲስ ማስረጃ እንዲካተት ማድረግ፤

፲፭ የሰዎችን የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሕገ-ወጥ መንገድ ወደ ሌላ ሰው እንዲዘዋወር ማድረግ ወይም እንዲዘዋወር መርዳት፤

10. Presenting a fraud document or information for officials or organs that have the authority to make a decision or fostering nepotism to prepare or allot or transfer lands, through lease or allotment, in contrary to the Proclamation, Regulation, or directive so that a decision will be made or reach a decision;

11. When an individual that competes in any urban land lease auction presents fraud evidence or assists the presentation of same, conceal information that he must describe or conspire with another competitor and undertake a fake competition;

12. Presenting a vacant land, without any construction, for name transfer or sale is contrary to the provisions of the relevant laws or trying to transfer a name or sell the land while knowing the land is vacant;

13. Illegally deduct and pay a tax, stamp tax, capital gain, and other service charges that one must pay in the process of name transfer;

14. Destroying landholding files or information from a file or adding irrelevant new evidence in the file;

15. Transferring the landholding assurance certificate of individuals to another person illegally or assist the transfer of same;

፲፮. የተሳሳተ የመሀንዲስ የመስክ ልኬት ማከናወን (ይዞታን በመጨመር ወይም በመቀነስ)፣

፲፯ መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎች ምርትን መገደብ፣ የንግድ ዕቃዎችን ማከማች ወይም የንግድ ዕቃዎች በመደበኛ የንግድ መስመር እንዳይሸጡ ለማድረግ መደበቅ፣ ማገድ ወይም መያዝ፣

፲፰ በህገ-ወጥ መንገድ የውጭ አገር ገንዘቦችን ማዘዋወርና ይዞ መገኘት፣

፲፱ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ገንዘብ ማተምና ማሰራጨት፤

፳ በሕገ-ወጥ መንገድ የጦር መሣሪያ ዝውውር ማከናወን፡፡

፯ **<u>የጥቆማ ወይም የመረጃ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት</u>**

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ ጥቆማና ተጨባጭ መረጃ የሚቀርብባቸው ሕገ-ወጥ ተግባራት እና ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸው ድርጊቶች አቀራረብ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

፩ ጥቆማ ያለው ማንኛውም መረጃ አቅራቢ ጥቆማውን በአካል፣ በቃል፣ በጽሁፍ ፣ በስልክ ፣ በፋክስ ፣ በኢሜል ወይም አመቺ በሆነ በማናቸውም ሌሎች መንገዶች ሊያቀርብ ይችላል፤

፪ ጥቆማው ለከንቲባ ጽህፈት ቤት ሲቀርብ፡-

ሀ) ጥቆማው የተፈፀመበት ተቋም እና አገልግሎት ሰጪው ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ስም ወይም ድርጊቱን የፈጸመው ሰው ስም ወይም ድርጊቱ የተፈጸመበት ቦታ (አድራሻ/ልዩ ቦታ መጠሪያው)፣

ለ) ጥቆማው የሚቀርብበትን ዋና ጉዳይ ፣

ሐ) ደጋፊ ማስረጃዎች ካሉ፣

መ) መንስኤ የሆነው ድርጊት የተፈፀመበትን ቀንና ቦታ፣

16. Carry out wrong engineering field measurements (either increasing or reducing landholdings);

17. Limiting basic merchandise products, storing business goods or hiding, limiting or holding back business goods so as not to sell it in the regular trade channels;

18. Illegal circulation of foreign currencies and possession ofthem;

19. Printing and distribution of local and foreign currencies;

20. Illegal dealings of firearms.

7. **<u>Reporting or Information Presentation Procedure</u>**

According to Article 6 of this Regulation, the presentation of reports and tangible evidence on illegal activities and other similar activities will be as follows:

1. Any informer who has information can report it in person, orally, in writing, through phone, fax, email, or any other convenient means.
2. When the report is presented to the office of the Mayor:
   a. the name of the institution where the report was taken place and the name of the employee or head that provided the service or the name of the person that committed the action or the place where the action took place (address/unique name of the place);
   b. the major issue of the report;
   c. supportive evidence, if there is any;
   d. the date and place where the cause of the action took place;

ሠ) መረጃ አቅራቢው ወይም ጠቋሚው ህገ-ወጥ ድርጊት ከፈጸመው ሰው ጋር ያለው ግንኙነት፣

ረ) በህገ ወጥ ተግባሩ ተሳታፊ ወይም ተካፋይ ናቸው ብሎ የሚጠረጥራቸው ሰዎችን ዝርዝር መረጃ ካለ፣

ሸ) የመረጃ አቅራቢው ሙሉ ስም እና አድራሻ፣

፫ ጽህፈት ቤቱ የጠቋሚውን ወይም መረጃ አቅራቢውን ጥቆማ ሲቀበል፡-

ሀ) የጥቆማው ጭብጥ ተለይቶ መያዙን ወይም መቀመጡን ያረጋግጣል፣

ለ) አግባብ ያላቸው መረጃዎች ካሉ አረጋግጦ ይቀበላል፣

ሐ) ጽህፈት ቤቱ በሚያዘጋጀው የባህር መዝገብ ላይ ይመዘግባል፣

መ) ጥቆማ የቀረበበት ጉዳይ የቀረበበት ቀንና ጊዜ ተጠቅሶ እንደ ጥቆማው አቀራረብ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለጠቋሚው ማረጋገጫ ይሰጣል፤

፬ ጥቆማውን የተቀበለው ጽህፈት ቤት የቀረበለትን መረጃ በ ፵፰ ሰዓት ውስጥ ጉዳዩን ለሚመረምረው ኃላፊ ማቅረብ ኖርበታል፡፡

## ፰ <u>የጥቆማ መልስ አሰጣጥ</u>

፩ ጥቆማውን እንዲቀበል የተመደበ ኃላፊ ወይም ተቋም ከህዝብ ወይም ከተገልጋይ ወይም ከማንኛውም መረጃ አቅራቢ የሚቀርብለትን ጥቆማ ጉዳዩን ላቀረበው መረጃ አቅራቢ ወይም ጠቋሚ ውሳኔውን መግለጽ ይኖርበታል፤

፪ ለጥቆማ አቅራቢዉ እንደየአግባቡ ውሳኔው በጽሁፍ ይገለጽለታል፤

e. the relationship the informer has with the person who committed the illegal activity;

f. detailed information about individuals that the informer suspects in involving or participating in the illegal activity, if there are any;

g. the full name and address of the informer.

3. When the office receives the report of an informer:

a. make sure thatthe gist of the report is specifically recorded and stated;

b. check and receive the relevant information;

c. record it on the registry that the office prepared;

d. make sure that confirmation is given to the informer by stating the date and time when the report was made if it is found necessary as per the presentation of the report.

4. The office that received the report should forward it within 48 hours to an official that will examine the case.

## 8. Providing Response for a Report

1. An official or institution that is assigned to receive a report, which comes to his attention from the public or customer or any other informer, should notify the decision to the informer that has brought the issue;

2. The decision will be notified to the informer through writing, as per the conditions;

፫ በጽሑፍ መልስ ለፈለገ ማንኛውም መረጃ አቅራቢ መልሱ የሚከተሉትን ሀሳቦች መያዝ አለበት፡-

ሀ) መረጃ አቅራቢው በዚህ ደንብ መሠረት ጥቆማውን ለሚያጣራው አካል ማድረሱን፣

ለ) ጥቆማው በሚገባ መጣራቱን፣

ሐ) በማጣራቱ ሂደት የተደረሰባቸው ግኝቶች፣

መ) ጥቆማው ትክክለኛ ካልሆነ አስፈላጊውን ማብራሪያ፣

ሠ) መረጃ አቅራቢው በመልሱ ወይም በተሰጠው ማብራሪያ ካልረካ ጥቆማውን ለማንና እስከ መቼ ማቅረብ እንደሚቻል፤

፬ የጥቆማውን ምላሽ በተመለከተ አስገዳጅ ሁኔታዎች ካልተፈጠሩ በስተቀር በዚህ ደንብ መሠረት ለሚቀርቡ ጥቆማዎች ከአሥር የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መልስ መሰጠት አለበት፤

፭ የጥቆማውን አፈጻጸም የሚከታተሉ የጽህፈት ቤቱ የስራ ክፍሎች ኃላፊዎች እና ሠራተኞች የመረጃ አቅራቢውን ወይም የጠቋሚውን ማንነትና ሚስጥራዊነት የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

**፱ <u>የመረጃ አመዘጋገብ ሂደት</u>**

፩ መረጃው የቀረበው በአካል ካልሆነ ጽህፈት ቤቱ መረጃ እንዲቀበል የተመደበው ባለሙያ መረጃውን በመቀበል የባህር መዝገብ ላይ ለሚመዘግበው የስራ ክፍል አቅርቦ ያስመዘግባል፤

፪ መረጃ አቅራቢው በግንባር ጽህፈት ቤት ድረስ መጥቶ ካቀረበ ወዲያውኑ በባህር መዝገብ ላይ ይመዘግባል፤ ለመረጃ አቅራቢውም መረጃ ማቅረቡን የሚገልጽ ማስረጃ ይሰጠዋል፤

3. For any informer who wants to have a written response, the response should include the following points:
   a. the informer, according to this Regulation, has submitted the report to the concerned organ that examines it;
   b. the report is examine accordingly;
   c. the findings obtained during the examination process;
   d. the relevant explanation if the report is not correct;
   e. to whom the informer will present his report and the duration when he is not satisfied with the given response or explanation;
4. Regarding the response to the report that was presented according to this Regulation, a response should be, without any force majeure, given within not more than ten working days;
5. Department heads and employees of the office that follow up the implementation of the report are obliged to keep the identity of the informer in secrecy.

**9. <u>Information Registration Process</u>**

1. If the information is not presented in person, the officer, assigned by the office to collect information, will receive the information and make sure its registration on the registry by the concerned department;
2. If the informer presents the information in person, it shall be registered immediately on the registry; confirmation will be provided to the informer for doing so;

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በግንባር ሳይቀርብ ጥቆማ የሰጠው ሰው በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ ወደ ጽህፈት ቤቱ በግንባር በመቅረብ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ የተዘረዘሩ መረጃዎችን በማቅረብ በባህረ መዝገብ ይመዘግባል፤

፬ ጽህፈት ቤቱ መረጃ እንደደረሰው ለመረጃ አቅራቢውም መረጃ ማቅረቡን የሚገልጽ ማስረጃ በ ፴ ደቂቃ ውስጥ የመረጃ አቅራቢነት ቅጽ ሞልቶ ይሰጠዋል፡፡

፲ **<u>መረጃው ተቀባይነት ስለሚያጣበት ሁኔታ</u>**

፩ ማንኛውም መረጃ ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከቱትን መረጃዎች አሟልቶ ያልቀረበ እንደሆነ ወይም፣

ለ) የቀረበው መረጃ ቀድም ብሎ በሌላ መረጃ አቅራቢ የቀረበ ከሆነ፣ ወይም

ሐ) መረጃው ከመቅረቡ በፊት ጽህፈት ቤቱ በራሱ የደረሰበት እንደሆነ፣ ወይም

መ) ጽህፈት ቤቱ ቀደም ብሎ መረጃ ደርሶት ምርመራ እያደረገበት ከሆነ፣

የቀረበው መረጃ ተቀባይነት አያገኝም፤

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (ሐ) የተደነገገው ቢኖርም ጽህፈት ቤቱ ያልደረሰበትና የተደበቀ ወይም የተሸፈነ አዲስ ሚስጥር ከሆነ መረጃው ተቀባይነት ይኖረዋል፤

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተቀባይነት የሌለው መረጃ ለጽህፈት ቤቱ የቀረበ እንደሆነ ይህንኑ ለመረጃ አቅራቢው በ ፭ የስራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ይገለጽለታል፡፡

3. The informer, who submitted a report according to Sub-Article (1) of this Article without appearing in person, should show up in person at the office within ten working days and cause the registration of the information enlisted under Article 7 of this Regulation on the registry;
4. When the office owns the information, it shall give evidence for the informer, within 30 minutes, for presenting it after filling the form of an informant.

**10. <u>Conditions that Invalidate the Information</u>**

1. Any information will not be valid if:

   a. it is not presented having all the indicated information under Sub-Article (2) of Article 7 of this Regulation; or

   b. it is already presented by another informer; or
   c. it is obtained by the office before the presentation of the information; or
   d. the office had already got the information and is investigating it;
2. Notwithstanding to letter (C) of Sub-Article (1) of this Article, the information will be acceptable if it is not unveiled by the office and a hidden new secret;
3. If a piece of invalid information is presented to the office according to Sub-Article (1) of this Article, such should be notified to the informer in writing within 5 working days.

## ፲፩ ለማበረታቻው ብቁ ስላለመሆን

፩ ጽህፈት ቤቱ ተቀባይነት ያገኘ ተጨባጭ መረጃ በሚከተሉት ሰዎች የሚቀርብ ከሆነ መረጃ አቅራቢው ለማበረታቻው ብቁ አይሆንም፡-

ሀ) በህገ-ወጥ ድርጊት ተካፋይ በሆነ ሰው የቀረበ ከሆነ፣

ለ) መረጃ አቅራቢው መረጃውን ለማቅረብ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ለጽህፈት ቤቱ የተሰጠውን ማስረጃ ካላቀረበ፣

ለማበረታቻ ብቁ አይሆንም፤

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) የተገለጸው ቢኖርም በራሳቸው ጥረት አስቀድሞ ሕገወጥ ድርጊቱን የጠቆመ ከሆነ ለማበረታቻው ብቁ ይሆናል፡፡

## ፲፪ የማበረታቻው መሠረት

፩ መረጃ ሰጪው ያቀረበው መረጃ በቀረበበት ጊዜ በጽህፈት ቤቱ ወይም አግባብ ባለው ተቋም በማይታወቅ ወይም ሊታወቅ ወይም ሊደረስበት የማይችል የተደበቀ ወይም የተሸፈነ መሆን አለበት፤

፪ ለተመዘገበው መረጃ ማበረታቻው የሚከፈለው መረጃው ከጽህፈት ቤቱ ወይም አግባብ ባለው ተቋም ተመርምሮ ተጨባጭ መረጃ መሆኑ ሲረጋገጥ እና ህገ-ወጥ ተግባሩ ሲከሽፍ ወይም ንብረቱ ሲመለስ ወይም ሕገወጥ ተግባሩ የመጨረሻ ውሳኔው ሲያገኝ ነው፤ የማበረታቻው መሰረት የሚሆነው በሰጠው መረጃ መሰረት በሚገኘው ውጤት ልክ ተሰልቶ ነው፤

፫ የማበረታቻ መሰረቱ የሚወሰነው በተሰጠው መረጃ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎች በመመርመር ይሆናል፤

## 11. Ineligibility for the Incentive

1. If the office obtains a shred of accepted, tangible evidence which was presented by the following individuals, the informer shall be ineligible:
   a. if it was presented by an individual who involved in the illegal activity;
   b. if the informer will not submit the information which was presented to the office according to Sub-Article (1) of Article 7 of this Regulation.
2. Notwithstanding to letter (a) of Sub-Article (1) of this Article, an informer that first reports the illegal activity on his own will, shall be eligible for the incentive.

## 12. Fundamental Principles of the Incentive

1. The information presented by the informer must be inaccessible, or hidden, or something that could not be known by the office or a relevant institution during its presentation;
2. The incentive for the registered report will be paid when the information is examined by the office or a relevant organ and such is confirmed as a tangible one; and if the illegal activity fails or if the property is returned or if a final decision is made on the illegal activity. The threshold for the incentive will be calculated as per the obtained resulted based on the information he has given;
3. The threshold for the incentive shall be decided by examining the submitted evidence on the given information;

፬ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም የቀረበው መረጃ ተጨባጭ መሆኑ ተረጋግጦ ነገር ግን በአስፈጻሚው የማስፈጸም ድክመት ምክንያት የመጨረሻ ውጤት ባያስገኝም ጥቆማ አቅራቢው ማበረታቻውን ማግኘት ይችላል፡፡

**፲፫ የማበረታቻው ምጣኔ**

መረጃ አቅራቢው የሰጠው ተጨባጭ መረጃ ያስገኘውን ውጤት መሠረት በማድረግ የማበረታቻው ምጣኔ ከዚህ በታች በተገለጸው ሁኔታ ይከፈላል፡-

፩ አግባብ ያለው አካል ሳይፈቅድ ማንኛውንም የከተማ መሬት መያዙን ወይም መወረሩን ወይም በመሬት ባንክ ተይዘው የነበሩ ይዞታዎችን ሕገወጥ በሆነ መንገድ መያዙን የጠቆመ ከሆነ በተጠቆመው ይዞታ ልኬት ስፋት ልክ በወቅቱ የሊዝ መነሻ ዋጋ ፲ (አሥር) በመቶ ማበረታቻ ያገኛል፤

፪ አግባብ ያለው አካል ፈቃድ ሳያገኝ በሕጋዊነት ከያዘው ይዞታ ጎን ያለን የከተማ ቦታ አስፋፍቶ መከለልና መጠቀም ወይም ማጠር ወይም ከአዋሳኝ ይዞታ ጋር ከቀላቀል ከተስፋፋው የይዞታ ልኬት ስፋት ልክ በወቅቱ የሊዝ መነሻ ዋጋ ፲ (አሥር) በመቶ ማበረታቻ ያገኛል፤

፫ በአካባቢ ልማት ፕላን መሠረት ለመንገድ አውታር፣ ለማህበራዊ ተቋማትና ለአረንጓዴ ሥፍራዎች አገልግሎት እንዲውሉ በተከለሉ ቦታዎች ላይ ያሉ በሕገ ወጥነት የተያዙና የተከለሉ ይዞታዎች መያዙን ሲጠቆም ከተያዘው የይዞታ ልኬት ስፋት ልክ በወቅቱ የሊዝ መነሻ ዋጋ ፲ (አሥር) በመቶ ክፍያ ያገኛል፤

4. Notwithstanding to Sub-Article (2) of this Article, the informer shall receive the incentive if the presented information is confirmed as a tangible one despite the implementation failure of the executive organ to attain the final result.

**13. The Proportion of the Incentive**

Based on the achieved results of the tangible evidence presented by the informer, the proportion of the incentive shall be paid as per the conditions listed below:

1. If the informer reports the seizure of an urban land without the permission of a relevant organ or land grabbing or illegal possession of landholdings occupied by the land bank, he shall get an incentive of 10 (ten) percent of the current initial lease price of the size of the informed holdings;
2. If the informer reports the use of urban land, which is adjacent to a legally occupied land through expansion and enclosing or making fences or combine it with a nearby landholding, he shall get an incentive of 10 (ten) percent of the current initial lease price of the size of the informed expansion landholdings;
3. If the informer reports an illegal seizure of lands that are demarcated for the purpose of road infrastructure, social institutions, and green areas on the local development plan, he shall get an incentive of 10 (ten) percent of the current initial lease price of the size of the informed occupied landholding;

፬ ለአካባቢ ጥበቃና ለአረንጓዴ ልማት፣ ፓርክ፣ የመንግሥት ይዞታዎች እና ለተለያየ አግልግሎት ተለይተው በተቀመጡ ባዶ ቦታዎች ላይ አግባብ ያለው አካል ሳይፈቀድ ለእቃ ማስቀመጫም ሆነ ሌላ ማንኛውም አግልግሎት አለአግባብ መያዙንሲጠቆም ከተያዘው የይዞታ ልኬት ስፋት ልክ በወቅቱ የሊዝ መነሻ ዋጋ ፲ (አሥር) በመቶ ክፍያ ያገኛል፤

፭ በግልጽ ባለቤት ሳይኖራቸው በህገ-ወጥ መንገድ ተግንብተው ያሉ ሕንጻዎች እና ታጠረው የተያዙ ባዶ ቦታዎችን ይዞ መገኘቱን ሲጠቆም ከተያዘው የይዞታ ልኬት ስፋት ልክ በወቅቱ የሊዝ መነሻ ዋጋ ፲ (አሥር) በመቶ ክፍያ ያገኛል፤

፮ በመንግስት ይዞታ ሥር የሚተዳደሩ ቤቶች፣ ሼዶችና ሌሎች ማንኛውም ይዞታዎችን በተሳሳተ ሰነድ ስም ማዞሩን ወይም ለማዞር መሞከሩን ሲጠቆም ከተያዘው የይዞታ ልኬት ስፋት ልክ በወቅቱ የሊዝ መነሻ ዋጋ ፲ (አሥር) በመቶ ማበረታቻ ያገኛል፤

፯ ከአዋጁ ውጪ የከተማ መሬትን መፍቀድ ወይም ማስተላለፍ ወይም ክልከላ እያለበት የይዞታ ምስክር ወረቀት ካርታ መስጠት ወይም ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ ይዞታ ማረጋገጥ ወይም የአርሶ አደር የሆነውን ይዞታ ለማይገባው ሰው መብት እንዲፈጠር ማድረጉን ሲጠቆም ከተያዘው የይዞታ ልኬት ስፋት ልክ በወቅቱ የሊዝ መነሻ ዋጋ ፲ (አሥር) በመቶ ማበረታቻ ያገኛል፤

4. If the informer reports inappropriate seizure of designated vacant spaces for the purpose of environmental protection and green development, parks, public holdings, and for various services and use same for storage or any other purposes without the permission of the relevant organ, he shall get an incentive of 10 (ten) percent of the current initial lease price of the size of the informed occupied landholding;
5. If the informer reports the seizure of buildings that are illegally constructed without having an identified ownership and protected and occupied vacant spaces, he shall get an incentive of 10 (ten) percent of the current initial lease price of the size of the occupied holdings;
6. If the informer reports naming transfer of houses, sheds, and any other landholdings that are under the administration of the government using fraud documents or an attempt to do so, he shall get an incentive of 10 (ten) percent of the current initial lease price of the size of the occupied landholding;
7. If the informer reports the granting of transfer of urban land or giving land holding certificate despite having restrictions or illegally verifying landholdings or create rights for the ineligible individual on the holdings of a farmer in contrary to the Proclamation, he shall get an incentive of 10 (ten) percent of the current initial lease price of the size of the occupied landholding;

፰. በሀሰተኛ ሰነድ የተዘጋጁ ካርታዎች፣ የግንባታ ፈቃዶች እና መሰል የመሬትና መሬት ነክ መረጃዎች ይዞ መገኘት ወይም ሀሰተኛ ሰነዶችን መሠረት አድርጎ ህገ-ወጥ ተግባር መፈጸሙን ሲጠቆም ከተያዘው የይዞታ ልኬት ስፋት ልክ በወቅቱ የሊዝ መነሻ ዋጋ ፲ (አሥር) በመቶ ማበረታቻ ያገኛል፤

፱. በመሬት፣ በመሬት ነክ እና በማናቸውም አስተዳደር አካላት ላይ የተመደበ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ጉቦ ሲቀባበል መገኘቱን ሲጠቆም ከተያዘው የይዞታ ልኬት ስፋት ልክ በወቅቱ የሊዝ መነሻ ዋጋ ፲ (አሥር) በመቶ ማበረታቻ ያገኛል፤

፲ አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያን ሳይከተል መሬትን በሊዝ ወይም በምደባ እንዲገኝ ሕጋዊ አስመስሎ መሬት እንዲዘጋጅ ወይም እንዲመደብ ወይም እንዲተላለፍ ለሥራ ኃላፊዎች ወይም ለመወሰን ስልጣን ለተሰጣቸው አካላት የተሳሳተ ሰነድ ወይም መረጃ ወይም አድሏዊ አሰራር በመከተል አቅርቦ በተሳሳተ መንገድ ማስወሰን ወይም መወሰኑን ሲጠቆም ከተያዘው የይዞታ ልኬት ስፋት ልክ በወቅቱ የሊዝ መነሻ ዋጋ ፲ (አሥር) በመቶ ማበረታቻ ያገኛል፤

፲፩ ማንኛውም በከተማ ቦታ ሊዝ ጨረታ የሚወዳደር ሰው የሀሰት ማስረጃ ካቀረበ ወይም እንዲያቀርብ ድጋፍ ካደረገ፣ መግለጽ የነበረበትን መረጃ ከደበቀ ወይም ከሌላ ተወዳዳሪ ጋር በመመሳጠር የሀሰት ውድድር ማድረጉን ሲጠቆም ከተያዘው የይዞታ ልኬት ስፋት ልክ በወቅቱ የሊዝ መነሻ ዋጋ ፲ (አሥር) በመቶ ማበረታቻ ያገኛል፤ የማበረታቻ መሰረቱ የሚወሰነው በተሰጠው መረጃ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎች በመመርመር ይሆናል፤

8. If the informer reports the possession of maps, construction permits, and similar land and land-related documents that are prepared using fraud documents or the execution of illegal activities based on fraud documents, he shall get an incentive of 10 (ten) percent of the current initial lease price of the size of the occupied landholding;

9. If the informer reports the taking of a bribe by an assigned official or employee on land, land-related, and any other administrative organ for his benefit or the benefit of another person, he shall get an incentive of 10 (ten) percent of the current initial lease price of the size of the occupied landholding;

10. If the informer reports the presence of a fraud document or information for officials or organs that have the authority to make a decision or the presence of nepotism to prepare or allot or transfer land, through lease or allotment, in contrary to the Proclamation, Regulation or directive so that a decision will be made or to reach a decision, he shall get an incentive of 10 (ten) percent of the current initial lease price of the size of the occupied landholding;

11. If the informer reports that an individual that contends in any urban land lease auction presents fraud evidence or assists the presentation of same, conceals a piece of information that must be described or conspire with another competitor and undertake fake competition, he shall get an incentive of 10 (ten) percent of the current initial lease price of the size of the occupied landholding;

፲፪. አግባብ ካለው የህግ ድንጋጌ ውጭ ግንባታ ያላረፈበትን ባዶ ቦታ ለስም ዝውውር ወይም ለሽያጭ ያቀረበ ወይም ባዶ ቦታ መሆኑን እያወቀ ሥም ዝውውር ለማድረግ ሙከራ ያደረገ ወይም ሽያጭ እንዲከናወን መደረጉን ከጠቆመ ሲጠቆም ከተያዘው የይዞታ ልኬት ስፋት ልክ በወቅቱ የሊዝ መነሻ ዋጋ ፲ (አሥር) በመቶ ማበረታቻ ያገኛል፤

፲፫ በስም ዝውውር መክፈል የሚገባውን የአሹራ፣ የቴምብር ቀረጥ፣ የካፒታል ጌይን እና ሌሎች የአገልግሎት ክፍያዎች ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ቀንሶ ማስከፍሉ ሲጠቁም ታጥቶ ገንዘብ ላይ ፲ (አሥር) በመቶ ማበረታቻ ያገኛል፤

፲፬ የይዞታ ማህደሮችን ወይም ከማህደር መረጃ ማጥፋት ወይም አግባብነት የሌለው አዲስ ማስረጃ እንዲካተት መደረጉን ሲጠቁም በዚህ ምክንያት የተገኘ ይዞታ መኖሩ ሲረጋገጥ ከተያዘው የይዞታ ልኬት ስፋት ልክ በወቅቱ የሊዝ መነሻ ዋጋ ፲ (አሥር) በመቶ ማበረታቻ ያገኛል፤

፲፭ የሰዎችን የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሕገ-ወጥ መንገድ ወደ ሌላ ሰው እንዲዘዋወር ማድረግ ወይም እንዲዘዋወር መርዳቱን ሲጠቁምና በመረጃ ሲረጋገጥ የብር ፶ሺ (ሃምሳ ሺህ ብር) ማበረታቻ ያገኛል፤

፲፮ የተሳሳተ የመሀንዲስ የመስክ ልኬት መከናወኑ እና የይዞታው ልኬት መጨመሩን ሲጠቆምና በመረጃ ሲረጋገጥ ተጨምሮ ከተያዘው የይዞታ ልኬት ስፋት ልክ በወቅቱ የሊዝ መነሻ ዋጋ ፲ (አሥር) በመቶ ማበረታቻ ያገኛል፤

12. If the informer reports the presence of vacant land, without any construction for name transfer or sale is contrary to the provisions of the relevant laws or an attempt to transfer a name or sell the land while knowing the land is vacant, he shall get an incentive of 10 (ten) percent of the current initial lease price of the size of the occupied landholding;
13. If the informer reports an illegal deduction and payment of tax, stamp tax, capital gain, and other service charges that one must pay in the process of name transfer, he shall get an incentive of 10 (ten) percent of the missing income;
14. If the informer reports the destroying of landholding files or information from a file or the inclusion of irrelevant new evidence in a file, and the confirmation of a landholding possession as a result of the thereof, he shall get an incentive of 10 (ten) percent of the current initial lease price of the size of the occupied landholding;
15. if the informer reports the transfer of a landholding assurance certificate of individuals to another person illegally or assist the transfer of same, and such is corroborated, he shall get an incentive of birr 50,000 (fifty thousand birr);
16. If the informer reports that a wrong engineering field measurement had been made and the size of the landholding was increased, and such is corroborated, he shall get an incentive of 10 (ten) percent of the current initial lease price of the size of the occupied landholding;

፲፯ መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎች ምርትን መገደብ፣ የንግድ ዕቃዎችን ማከማቸት ወይም የንግድ ዕቃዎች በመደበኛ የንግድ መስመር እንዳይሸጡ ለማድረግ መደበቅ፣ ማገድ ወይም መያዙ ከተጠቆመና በማስረጃ ሲረጋገጥ የዕቃውን ዋጋ ፫ (ሶስት) በመቶ የገንዘብ ማበረታቻ ያገኛል፤

፲፰ በህገ-ወጥ መንገድ የውጭ ምንዛሬ ማዘዋወርና ይዞ መገኘቱን ከጠቆመ ከተገኘው የገንዝብ መጠን ላይ ፲ (አሥር) በመቶ በኢትዮጵያ ብር በወቅቱ ምንዛሬ ተመን ማበረታቻ ያኛል፣

፲፱. የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ገንዘብ ማተምና መሰራጨቱን ከተጠቆመና በማስረጃ ከተረጋገጠ ብር ፶ሺ (ሃምሳ ሺህ ብር) ማበረታቻ ያገኛል፤

፳ በሕገ-ወጥ መንገድ የጦር መሣሪያ ዝውውር ማከናወኑን ከጠቆመና በማስረጃ ከተረጋገጠ ብር ፶ሺ (ሃምሳ ሺህ ብር) ማበረታቻ ያገኛል፡፡

**፲፬ ማበረታቻውን ተመላሽ ስለማድረግ**

በማናቸውም ሁኔታ በስህተት ወይም አላግባብ የተከፈለ ማበረታቻ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ መቋቋም፣ አደረጃጀት እና ቅሬታ አቀራረብ

**፲፭የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ስለማቋቋም**

፩ በዚህ ድንብ መሠረት ከመረጃ አቀራረብና ከማበረታቻ አሰጣጥ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ቅሬታዎችን መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ይቋቋማል፤

17. If the informer reports actions of limiting basic merchandise products, storing business goods or hiding, limiting or holding back business goods so as not to sell it in the regular business channels, and such is corroborated, he shall get an incentive of 3 (three) percent of the price of the goods in cash;
18. If the informer reports the illegal circulation of foreign currencies and its possession, he shall get an incentive of 10 (ten) percent of the amount of the confiscated money in birr as per the existing foreign currency rate;
19. If the informer reports the printing and distribution of local and foreign currencies, and such is corroborated, he shall get an incentive of birr 50,000 (fifty thousand birr);
20. If the informer reports the illegal circulation of firearms, and such is corroborated, he shall get an incentive of birr 50,000 (fifty thousand birr).

**14. Returning the Incentive**

In any condition, a wrongly or inappropriately paid incentive shall be returned.

## PART THREE

## COMPLAINT HEARING COMMITTEE ESTABLISHMENT, ORGANIZATION AND COMPLAINT SUBMITTAL PROCEDURE

**15. Establishment of Complaint Hearing Committee**

1. A complaint hearing committee that will investigate complaints related to the presentation of information and incentive delivery as per this Regulation and forward a decision proposal will be established.

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቋቋመው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ተጠሪነት ለጽህፈት ቤት ኃላፊ ይሆናል፡፡

**፲፮ <u>የኮሚቴው አደረጃጀት</u>**

በዚህ ድንብ መሠረት የሚቋቋመው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ እንደሚከተለው ይደራጃል፡-

፩ በጽህፈት ቤት ኃላፊ የሚመደብ ሰብሳቢ እና ከተለያዩ የስራ ክፍሎች የተውጣጡ አራት አባላት ይኖሩታል፤

፪ ከየሥራ ክፍሎቹ የሚሰየሙት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት የሙያ እና የጾታ ስብጥር ኖሯቸው እንዲደራጁ ይደረጋል፤

፫ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ፀሐፊ ከኮሚቴው አባላት ውስጥ በጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ይሰየማል፡፡

**፲፯. <u>ስለቅሬታ አቀራብ</u>**

በዚህ ድንብ መሠረት ከማበረታቻ እና ከመረጃ አቀራረብና አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ቅሬታዎች አቀራረብ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

፩ ያቀረብኩት መረጃ አልተመዘገበልኝም ወይም ከማበረታቻ አሰጣጥ ጋር ተያይዞ ቅሬታ አለኝ የሚል ቅሬታ አቅራቢ ለቅሬታው መንስኤ የሆነው ጉዳይ በተወሰነ በአሥር ቀናት ውስጥ ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል፤

፪ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ውሳኔዎችን የሚሰጠው ደንቡን ተከትሎ ይሆናል፤

፫ ቅሬታውን የማጣራት ስራ በሚከተለው አግባብ መከናወን ይኖርበታል፡-

ሀ) እንደ አስፈላጊነቱ ከባለጉዳዩ ጋር በመወያየት፣

ለ) ቅሬታውን ፈጥረዋል ተብሎ ቅሬታ ከቀረበበት መዝጋቢ አካል ጋር ወይም ቅሬታ በተፈጠረበት አካባቢ በግንባር በመቅረብ፣

2. The complaint hearing committee which will be established according to Sub-Article (1) of this Article shall be accountable to the head of the office.

**16. <u>Organization of the Committee</u>**

The complaint hearing committee shall be established as follows:

1. It shall have a chairperson assigned by the head of the office and four individuals drawn from different departments;
2. The organization of the members of the complaint hearing committee drawn from the various departments shall consider professional and gender integration;
3. The secretary of the complaint hearing committee shall be assigned by the head of the office among the members of the committee.

**17. <u>Complaint Submittal Procedure</u>**

Complaints related to the presentation of information incentive delivery as per the Regulation shall be presented as per the following complaint submittal procedure:

1. A complainant, having unrecorded information or who has a complaint in connection with incentive delivery, may present his complaint to the complainthearing committee within ten days after a decision is made on the case that causes the thereof;
2. The complaint hearing committee shall pass its decision through complying with the Regulation;
3. The investigation of the complaint shall be carried out as per the following procedure:

   a. discuss with the complainant, when it is found necessary;

   b. discuss with the organ that the complaint has been lodged against or present in person at the place where the issue occurred;

ሐ) አስፈላጊ የሆኑ የሰነድ ማስረጃዎች እንዲቀርቡ በማዘዝ ወይም በመመርመር ሊያጣራ ይችላል፣

፬ የኮሚቴው ውሳኔ የአብላጫ ድምጽ ስርዓት የሚከተል ይሆናል፣

፭ ኮሚቴው የሚነሱትን ቅሬታዎች በአግባቡ በመመዝገብና ቃለ-ጉባዔ በመያዝ ይህንን ደንብ መሠረት በማድረግ የውሳኔ ሀሳብ በማዘጋጀት ለጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ያቀርባል፤

፮ ኮሚቴው ለቀረበለት አቤቱታ መረጃዎችን በማሰባሰብና በማጣራት ቅሬታው በቀረበለት በአምስት ቀን ውስጥ ውሳኔውን በፅሁፍ ለቅሬታ አቅራቢው ይሰጣል፤

፯ በውሳኔው ቅር የተሰኘ ቅሬታ አቅራቢ ለከተማው ከንቲባ ማቅረብ ይችላል፤ ውሳኔውም የመጨረሻ ይሆናል፤

፰ ኮሚቴው ያለአግባብ በሚሰጠው ውሳኔ በጋራም ሆነ በተናጠል በህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት
## የመረጃ አያያዝና አጠባበቅ እና የመረጃ አቅረቢና መዝጋቢ ተግባርና ኃላፊነት

### ፲፰ የመረጃ አያያዝና አጠባበቅ

፩ መረጃ ምዝገባው በሃርድና በሶፍት ቅጂ የሚከናወን ሲሆን ለሃርድ ኮፒው ምዝገባ የሚያገለግለው ባህር መዝገብ በጽህፈት ቤት አንድ ወጥ ቅጽ አስፈላጊ ዝርዝሮች በመያዝ በቁጥር ቅደም ተከተል ተመዝግቦ የሚያዝ ይሆናል፤

፪ ጽህፈት ቤቱ መዝግቦ የያዘውን የመረጃ አቅራቢ የምዝገባ መረጃ በሃርድና በሶፍት ኮፒ አደራጅቶ ይያዛል፤

c. order the presentation of the necessary evidence and examine it;

4. The decision of the committee shall be passed through majority vote;
5. The committee shall properly record the raised complaints and keep minutes; and prepare a decision proposal according to this Regulation and submit same to the head of the office;
6. The committee shall collect and examine the information regarding the presented complaint and provide its decision to the complainant in writing within five days;
7. A complainant who is dissatisfied with the decision may present his case to the Mayor, and the decision will be final;
8. The committee will be held accountable, individually or collectively, for the decision it passes inappropriately.

## PART FOUR
## INFORMATION RESERVATION AND SECURITY, AND DUTIES AND RESPONSIBILITIES OF THE INFORMER AND RECORD OFFICER

### 18. Information Reservation and Security

1. The registration of the information shall be carried out in soft and hard copies, and the registry for the registration of the hard copy at the office shall be prepared in a similar format having the necessary details, and it will be recorded and kept in a numerical sequential manner;
2. The office shall organize and retain the already recorded registration information of the informer in hard and soft copies;

፫ የመረጃውን ደህንነት ለመጠበቅና እያንዳንዱ ምዝገባ መጠባበቂያ መረጃ ወይም ባክአፕ እንዲኖረው ለማድረግ ሃርድ ኮፒውን በተመለከተ ባህር መዝገብ የኮምፒውተር ማጠቃለያ እንዲቀመጥ ተደርጎ ደህንነቱ ይጠበቃል፤

፬ የመረጃውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዘው ኦዲት ይደረጋል፤

፭ በሃርድ ቅጅውና በሶፍት ቅጅው መረጃ መካካል ልዩነት ቢፈጠር የሃርድ ቅጅው መረጃ እንደ ትክክለኛ መረጃ የሚቆጠር ይሆናል፡፡

**፲፱ የመረጃ አቅራቢው ኃላፊነትና ተጠያቂነት**

፩ መረጃ አቅራቢው በጽህፈት ቤቱ ጥሪ ከቀረበለት ጊዜ ጀምሮ በ ፮ (ስድስት) ወር ጊዜ ውስጥ የተሰጠውን ቅጽ በመያዝ ቀርቦ ክፍያውን መቀበል አለበት፤

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ መቅረብ ያልቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ካስረዳና መረጃ ካቀረበ የክፍያው ጊዜ ገደብ ለተጨማሪ አንድ ወር ብቻ ሊራዘምለት ይችላል፤

፫ ማንኛውም መረጃ አቅራቢ ጽህፈት ቤቱን በማታለል ወይም በማጭበርበር የተከፈለውን ማበረታቻ በዚህ ድንብ አንቀጽ ፲፬ መሠረት ተመላሽ ማድረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፤

፬ ማንኛውም ጠቋሚ ወይም መረጃ አቅራቢ የሚያቀርበው መረጃ ትክክለኛና በእውነት ላይ የተመሠረተ መሆን ይኖርበታል፤ የተሳሳተ መረጃ ማቅረብ በሕግ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

**፳ የጽህፈት ቤቱ ኃላፊነት**

፩ ይህን ድንብ የሚያስፈጽም የሥራ ክፍል በጽህፈት ቤቱ ሥር ያደራጃል፤

፪ የጥቆማ መስጫ የስልክ ጥሪ ማዕከል ያደራጃል፤

3. To secure information and to have a backup for each registration, regarding the hard copy, a computerized summary will be prepared for the registry to ensure its security;
4. A periodical audit will be carried out to ensure the accuracy of the information as it is found necessary;
5. If there is a contradiction between the hard and soft copy of the information, the information on the hard copy will be taken as the accurate one.

**19. Duties and Responsibilities of the Informer**

1. The informer should appear in person having the form that was given to him and receive his payment with 6 (six) months starting from the day the office summoned him;
2. If the informer could not appear within the stated period under Sub-Article (1) of this Article due to force majeure and explain it and bring evidence for the thereof, the payment period might only be extended for one month;
3. Without prejudice to Article 14 of this Regulation that returning the incentive the informer through treachery or deceiving the office, he shall be held accountable by the relevant laws;
4. The information of any informer should be accurate and based on reality; providing fake information entails accountability.

**20. Responsibility of the Office**

1. Establish a department that implements this Regulation under the office;
2. Establish a call center for providing a report;

፫. የቀረበለት መረጃ ተቀባይነት ያለው ከሆነ በደንቡ አንቀጽ ፯ መሠረት ይመዘግባል፤

፬. በቀረበው መረጃ መነሻነት ህገወጥ ተግባር መኖሩና መረጋገጡ እና ውጤት ማምጣቱ ሲታወቅ በ ፫ የስራ ቀናት ውስጥ የመረጃ አቅራቢውን ማንነት ሚስጥራዊነት በጠበቀ ሁኔታ ወይም በስልክ በደብዳቤ እና በሌሎች አመቺ ዘዴዎች ጥሪ ያደርጋል፤

፭. ጥቆማ የተሰጠበት ጉዳይ በገንዘብ በቀላሉ መተመን የሚያስቸግር ከሆነ ጽህፈት ቤቱ አግባብነት ካላቸው ተቋማት ጋር በመተባበር ዋጋ የሚተምን ጊዚያዊ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል፤

፮. የጠቋሚውን የጥቆማ ደረጃ በማስወሰን ለክፍያ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን እና ተከፋይ የሚሆነውን የገንዘብ መጠን በመግለጽ ለመረጃ አቅራቢው ክፍያ እንዲፈጸም ለክፍያ ዳይሬክቶሬት ደብዳቤ ይጽፋል፤

፯. መረጃ አቅራቢው ያስመዘገበው መረጃም ሆነ የአያያዘው ማስረጃ የተጭበረበረ ወይም ስህተት መሆኑ ከተረጋገጠ የወንጀል ኃላፊነት ማስከተሉ እንደተጠበቀ ሆኖ ጽህፈት ቤቱ መረጃ አቅራቢውን ከተጠቃሚነት ይሰርዘዋል፤

፰. ጽህፈት ቤቱ መረጃ አቅራቢዎች በጠቋሚነታቸው ምክንያት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሚደርስባቸው አደጋና ጥቃት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ከለላ እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፤

፱. ጽህፈት ቤቱ ለማበረታቻ አሰጣጡ አስፈላጊ መረጃዎችና ሰነዶች መሟላታቸው በየደረጃው ባለው ሠራተኛና የሥራ ኃላፊ ተረጋግጦ ሲቀርብለት በአስተዳደሩ ፋይናንስ ሕግ መሠረት ለተጨባጭ መረጃ አቅራቢ በደንብ ው የተጠቀሰውን ማበረታቻ ይከፍላል፤

3. It shall record the submitted information according to Article 7 of this Regulation if it is found acceptable;

4. If the presence of the illegal activity is confirmed and it has given a result, the office shall summon the informer through phone, letter or any convenient means by keeping the identity of the informer in secrecy;

5. If it is difficult to estimate the worth of the reported case in cash, the office may establish a temporary committee in collaboration with the relevant organs that estimate the value of it;

6. Cause the level of the informer to be decided, state the necessary documents to make the payment and the amount; and write a letter to the finance directorate to effect the payment for the informer;

7. If the recorded information or attached evidence of the informer is confirmed deceitful or fraud, the office shall revoke the informer from eligibility without prejudice to the criminal liability of the thereof;

8. The office shall support informers to get protection, according to the relevant laws, from the possible danger and assault as a result of being an informant;

9. The office shall pay the stated incentive on the Regulation for informers that has brought tangible evidence according to the finance laws of the city government upon the submittal of the necessary documents for the provision of incentives and the confirmation of the thereof by employees and heads at every level;

፲. ስለ ተጫባጭ መረጃ አቅራቢዎች፣ በዓመት ውስጥ በቀረበው መረጃ መነሻነት የተጠቆመው ህገወጥ ተግባር ላይ የእርምት እርምጃ ተወስዶ ወደ ቀድሞው ቦታ መመለሱ ወይም መታረሙን እና ለመረጃ አቅራቢዎቹ የተሰጠውን የማበረታቻ መጠን እንዲሁም በአጠቃላይ የስራ አፈጻጸሙን ሪፖርት ለከንቲባው ያቀርባል፡፡

**፳፩ መረጃውን የሚቀበለው ባለሙያ ኃላፊነት**

ጥቆማውን የተቀበለው ባለሙያ፡-

፩ ህገወጥ ድርጊትን በተመለከተ ጥቆማ ሲደርሰው የመቀበል ግዴታ አለበት፤

፪ ጽህፈት ቤቱ ባዘጋጀው የመመዝገቢያ ቅጽ መሠረት መረጃውን ይቀበላል፤

፫ የተቀበለውን መረጃ ወዲያውኑ በተዘጋጀው ባህረ መዝገብና የኮምፒውተር ፕሮግራም ውስጥ ይገለብጣል እንዲሁም የመረጃውን ሂደት በየደረጃው እየተከታተለ ይመዘግባል፤ ይይዛል፤

፬ መዝጋቢው አካል ለመዘገባቸው መረጃዎች አያያዝ አስተዳደርና ደህንነት ኃላፊነት አለበት፤

፭ የተቀበለውን መረጃ እና የመረጃ ሰጪውን ሚስጥራዊነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

**ክፍል አምስት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**፳፪ የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

10. Present reports about informers that submitted tangible information, the measures taken on the illegal activities based on the given reports and the return of same to its prior condition and rectification, and the amount of incentives given for informers as well as a general performance report to the Mayor.

**21. Responsibilities of the Record Officer**

1. Has the obligation to receive a report regarding an illegal activity;
2. Receive the information on the registration format which is prepared by the office;
3. Copy the information he received immediately on the registry and computer program; and follow-up, record, and hold the process of the information at every level;
4. Has the responsibility for the management and security of the information that is recorded by the concerned organ for the registration;
5. Has the obligation to keep the information he received and the identity of the informer in secret.

**PART FIVE**

**MISCELLANEOUS PROVISIONS**

**22. Duty to Cooperate**

Any individual shall be duty-bound for the implementation of this Regulation.

**፳፫ ተጠያቂነት**

ማንኛውም ሰው የዚህን ደንብ ድንጋጌ ተላልፎ ቢገኝ እንደሁኔታው በአስተዳደር ውሳኔ፣ አግባብ ባላቸው ሕጎች በወንጀል ወይም በፍትሐ፡ ብሔር ሕግ ወይም በሁለቱም ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**፳፬ ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ደንቦች**

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማናቸውም የከተማ ካቢኔ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፭ መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ጽህፈት ቤቱ ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስችል መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

**፳፮ ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከነሐሴ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፰ ፪ሺ፲፫ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ**



**23. Accountability**

Any person that contravenes the provisions of this Regulation shall be held accountable by, as per the conditions, administrative decision, the relevant criminal laws or civil laws, or both.

**24. Inapplicable Laws**

Any Regulation, directives, or customary practices of the city government which are inconsistent with his Regulation, shall have no effect.

**25. Power to Issue Directives**

The Office may issue directives for the implementation of this Regulation.

**26. Effective Date**

This Regulation shall enter into force as of this $24^{th}$ day of August 2021.

**Done at Addis Ababa, this $24^{th}$ day of August 2021**

**Adanech Abiebie**

**Deputy Mayor of Addis Ababa City**